# የኤሌክትሪክ አቅርቦት የዋጋ ለውጥን በተመለከተ ከ Cambridge ከተማ አስተዳደር የተሰጠ አስፈላጊ መልዕክት

ታህሳስ (December) 18 ቀን 2025

**የኤሌክትሪክ ሂሳቦ፤ በከተማችን** በቡድን ኤሌክትሪሲቲ የመግዛት ፕሮግራምን በሚያካተተው **በ Cambridge Community Electricity\ ውስጥ የተመዘገበ ነው።** በስቴት (ክፍለሃገር) ህግ መሰረት፣ የአብዛኛዎቹ ደንበኞቻችን ምዝገባ በኦቶማቲክ መንገድ ይከናወናል፡፡

በዚህ ፕሮግራም፤ ከ Eversource ስታገኙት የቆዩት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፤ በ Cambridge ዋጋ የተተመነ ነበር፤ እርሶ የተመዘገቡት **100% Green** ኦፕሽን በመባል በሚታወቀው ነው፡፡ ይህም ማለት በፕሮግራሙ ከሚያገኙት ኤሌክትሪሲቲ ውስጥ 100% ውን ከአዲስ የሚታደስ የሃይል ማመንጫ ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

ከሚመጣው ጥር ወር (January) ጀምሮ **ዝቅ ያለ ዋጋ** ይከፍላሉ፡፡

- በአሁኑ ወቅት የሚከፍሉት የኤሌክትሪክ ዋጋ ለአንድ ኪሎዋት 16.82 ¢/kWh። አዲሱ ዋጋ ደግሞ **14.90 ¢/kWh** ይሆናል።
- አዲሱ ዋጋ የሚጀመረው ጥር (January) 2026 ሲሆን እስከ ጥር (January) 2029 ይዘልቃል፡፡
- አዲሱ ዋጋ፤ Eversource ለመኖርያ ቤቶች ካቀረበውና የካቲት (February) 1 ቀን 2026 በስራ ከሚተገበረው ለአንድ ኪሎዋት 15.065 ¢/kWh የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ **ዝቅ** ያለ ነው፡፡ የ Eversource ዋጋዎችን በሙሉ ለማየት በስተጀርባ ይመልከቱ።
  የ Eversource ዋጋዎች በየግዜው ስለሚቀያየሩና በመጪው ግዜያት ዋጋዎቹ ምን ያህል እንደሚሆኑ በትክክል ስለማይታወቅ፤ ከ Eversource ጋር ወደፊት የገንዘብ ቁጠባ (savings) ለማድረግ ዋስትና የለም።

አዲሱና ዝቀተኛው የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ፡

**14.90 ¢ /kWh**

ይህንን በየካቲት (February) ወር ክፍያዎ ላይ ይመልከቱት

ለሂሳብ ቁጥር፡

የደንበኞች እገዛ፡ **844-379-9934**

ተጨማሪ መረጃና የራስ አገልግሎት (self service):
**CambridgeMA.gov/enrollCCE**

## ውሳኔው የእርሶ ነው። ለራስዎ ትክክል ነው የሚሉትን ይምረጡ።

- **በዚህ መካፈሉን ለመቀጠል ከወሰኑ፤** በ100% Green አማራጭ የሚያደርጉት ምዝገባ ለአንድ ኪሎዋት **14.90 ¢/kWh** ክፍያ በኦቶማቲክ መንገድ በጥር (January) ወር ላይ ይጀመራል፡፡ ይህንንም በየካቲት ወር (February) የክፍያ ወረቀት ላይ ማየት ይችላሉ፡፡
- **በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉትን ምርጫ ለመቀየር ከፈለጉ፤** ከአዲሶቹ የሚታደሱ አማራጮች ውስጥ ከኤሌክትሪኮ 75%ውን ለማግኘት ከፈለጉ Standard Green የተባለውን አማራጭ ይምረጡ። አነስተኛ ዋጋ ከፈለጉ Economy ይምረጡ፡፡ የተተመኑት ዋጋዎች በሙሉ ከጥር ወር (January) 2026 እስከ ጥር ወር (January) 2029 የሚዘልቁ ናቸው።

ሂሳቦ በኦቶማቲክ መንገድ እዚህ ላይ ይታደሳል፡፡

| 14.90 ¢/kWh | 14.48 ¢/kWh | 13.77 ¢/kWh |
|---|---|---|
| 100% GREEN | STANDARD GREEN | ECONOMY |
| 100% ከአዲሶቹ የሚታደሱ ምንጮች | 75% ከአዲሶቹ የሚታደሱ ምንጮች | ዝቅተኛው የፕሮግራሙ ዋጋ |

- **ከፕሮግራሙ መውጣት ከፈለጉ፡** Yካለምንም ክፍያ ወይም መቀጮ ከፕሮግራሙ መውጣት ይችላሉ፣ የ Eversource ወቅታዊ Basic Service ዋጋ ማግኘት ወይም ከማንኛውም ሌላ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅራቢ ጋር ውል መፈራረም ይችላሉ። የ Eversource ወቅታዊ ዋጋዎችን ዝርዝር ለማየት በስተጀርባ ይመልከቱ።

**ሌላ የፕሮግራም አማራጭ ለመምረጥ ወይም ከፕሮግራሙ ለመውጣት፤ CambridgeMA.gov/enrollCCE ይጎብኙ። ወይም ወደ ደንበኞች እገዛ ክፍል በስልክ ቁጥር 844-379-9934 በመደወል ከከተማው የፕሮግራም አማካሪዎች ጋር ተገናኙ።**

## የ Cambridge 100% Green ማወዳደርያ ▼      ከፕሮግራሙ ከወጡ ▼

| 100% GREEN | የወቅቱ ዋጋዎ | አዲሱ ዋጋዎ | በ Eversource Basic Service የቀረቡ ዋጋዎች |
|---|---|---|---|
| ዋጋ | **16.82 ¢/kWh** | **14.90 ¢/kWh** | **15.065 ¢/kWh** - መኖርያ ቤቶች<br>**14.466 ¢/kWh** - ትናንሽ የንግድ ቤቶች<br>**17.329 ¢/kWh** - ትላልቅ የንግድ ቤቶች |
| **የዋጋው የሚዘልቅበት የግዜ ገደብ** | ከጥር (January) 2024 እስከ ታህሳስ (December) 2025 | ከጥር (January) 2026 እስከ ጥር (January) 2029 | ጥር (February) 1 ቀን እስከ ሓምሌ (July) 31 ቀን 2026 - መኖርያ ቤቶችና ትናንሽ የንግድ ቤቶች<br>ከየካቲት (February) 1 ቀን እስከ ሚያዝያ (April) 30 ቀን 2026 - ትላልቅ የንግድ ቤቶች |
| **ከአዲስ የሚታደሱ የሃይል ማመንጫዎች የሚገኝ ኤሌክትሪሲቲ ከአጠቃላዩ %*** | | | |
| በ Cambridge የተጨመረ | 73% | 70% | - |
| በስቴት ህግ (state law) የሚጠየቅ (ኤሜ ክፍል 1 ረጨት (MA Class I RECs) | 27% | 30% | 30% |
| **ጠቅላላ** | **100%** | **100%** | **30%** |

* በሰንጠረዡ እንደሚታየው የሚታደስ ኤነርጂ መግዛትን በተመለከተ፤ የፕሮግራሙ ኤሌክትሪሲቲ አቅራቢ፤ በተጨማሪ ከሌሎች ንጹህ ወይም የሚታደሱ ማመንጫዎች ረጨ (REC) እንዲገዛ የክፍለሃገሩ ህግ ይጠይቃል። ይህ ግገርም ተካፋዮች ከሚጠቀሙት ኤሌክትሪክ 39% ጋር መስማማት አለበት።

## ተጨማሪ መረጃ፤

- **የ Cambridge Community Electricity፤ ፕሮግራሙ ከተመሰረተ ከ2017 ጀምሮ፤ ከ Eversource ዋጋዎች ጋር ሲወዳደር፤ ተሳታፊዎች ከ$95 ሚልዮን በላይ እንድያጠራቅሙ (save) አድርጓል።** ይሁንና የ Eversource ዋጋዎች በየግዜው ስለሚለዋወጡና ወደፊት የሚደረጉት ዋጋዎች ስለማይታወቁ፤ **በመጪው ግዜያት የገንዘብ ቁጠባ ለማድረግ ዋስትና የለም።**
- **በፕሮግራሙ የሚሳተፉት ሁሉ፤ አዲስ በሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል እድገት ላይ በቀጥታ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።** ሁሉም ተካፋዮች፤ በ Cambridge በሚገኘው Graham and Parks Elementary School ውስጥ ከጸሃይ በሚመነጭ ሃይል (solar) ለሚደረጉ ፕሮጀክቶች ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። በተጨማሪም Standard Green እና የ100% Green ፕሮግራም ተሳታፊዎች፤ በ Illinois ከጸሃይ ከሚገኝ ሃይል፤ በ North Dakota ደግሞ በነፋስ ሃይል የሚመሰረቱ አዲስ ፕሮጀክቶች እንዲጎለብቱ አዝዛቸውን አድርገዋል። እነኚህ ፕሮጀክቶች የሚገኙት የኤሌክትሪክ መረቦች (electric grids) ባሉበትና የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ሃይል ደግሞ በ New England ይወጣ ከነበረው የካርበን ልቀት (emissions) የበለጠ በመሆኑ፣ እነዚህ ንጹህ ፕሮጀክቶች በ New England ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የበለጠ ልቀት እንዳይኖር የሚያግዱ ናቸው። የ Standard Green እና የ 100% Green ፕሮግራም ተሳታፊዎች ክፍለሃገሩ ከሚጠይቃቸው እኩል ወይም ከዛ በላይ ተጨማሪ የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል የምስክር ወረቀቶችን ያገኛሉ።
- **የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚያደርግሎት፤** ለማህበረሰባችን እጅግ በጣም ጥሩ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየው **Direct Energy Services, LLC ("Direct Energy")** መሆኑን ይቀጥላል። በሚላክሎ የክፍያ ወረቀት ላይ የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ዳይሬክት ኤነርጂ "Cambridge Comm Elec Direct Energy" የሚል በቀጣይነት ያያሉ። እንደወትሮው፤ ኤሌክትሪሲቲን በተመለከተ ያሎት የመጀመርያው ዝምድና ከ Eversource ጋር ነው። በመሆኑም መብራት ሲጠፋቦት ወይም የኤሌክቲርክ ሃይል ሲቋረጥቦት ሁሌም ቢሆን እነርሱ ጋ መደዎሎን ይቀጥሉ። በተጨማሪም Eversource የኤሌክትሪክ ክፍያዎን ወረቀት ለእርሶ መላኩን ይቀጥላል። እንደ አንድ የ Cambridge Community Electricity አባል መጠን የሚያገኙት የክፍያ ወረቀት ይሄው ብቻ ነው።
- **ከ Direct Energy ጋር የተደረገው ስምምነት ሲያበቃ፤** የከተማው አስተዳደር ሌላ የረጂም ግዜ ውል ለመፈራረም ዕቅድ አለው። የኤሌክትሪክ አቅርቦት የሚያደርገውና የሚታደሰው የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት ሊለወጥ ይችላል፤ የሚከፈለው ዋጋም አሁን ካለው ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል። አስቀድመው ካላሳወቁ በስተቀር፤ ባሎት የፕሮግራም አማራጭ ውስጥ ሆነው አዲሱን ዋጋ መክፈል ይቀጥላሉ። የከተማይቱ አስተዳደር እንዲህ ዓይነቱ ለውጦች ሲኖሩ፤ ለውጦቹ በስራ ላይ ከመተግበራቸው በፊት ከፕሮግራሙ ለመውጣት ወይም ሌላ አማራጭ እንዲወስዱ ቀደም ብሎ ማስታወቅያ ይሰጣል።

## እራሶን ከኤሌክትሪሲቲ አጭበርባሪዎች/አታላዮች (scams) እራስዎን ይጠብቁ!

▶ ምንም እንኳን ከ Eversource ጋር ነው የምንሰራው ቢሉም፤ ስልክ ደውለው ገንዘብ ወይም የስጦታ ካርድ የሚጠይቆትን ሰዎች ተጠራጠሩ። ከማን ጋር በመነጋገር ላይ መሆንዎን ካላወቁ፤ ስልኩን ይዝጉና ወደ Eversource ደውለው ሂሳቦት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያረጋግጡ።